*የኢሕአፓ አመራር አባል አቶ ፋሲካ በለጠ በዋሽንግተን ዲሲ በተደረገው የኢሕአፓ 36 ኛ በዓል ላይ ያስተላለፉት መልእክት*

ክቡራን እናቶች÷ አባቶች÷ ወንድሞች÷ እህቶች ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች÷ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች- ጥሪያችንን አክብራችሁ በዓሉን ከእኛ ጋር ለማክበር እዚህ በመገኘታችሁ በኢሕአፓ ስም ÷ በአመራሩና በአባላቱ ስም ከፍ ያለ ምስጋና ማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡ ይህንን በዓል ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥረት ያደረጉትን በዲሲና አካባቢው የሚገኙ የኢሕአፓ ኮሚቴና አባላትንም አመሰግናለሁ፡፡

በዛሬው ቀን የኢሕአፓን 36ኛ በዓል የምናከብረው የልደት ሻማ አብርተንና ኬክ ቆርሰን ለመደሰትና ለመዝናናት አይደለም፤ ብዙ ዓመትታ በማስቆጠራችንም ራሳችንን ከፍ ከፍ አድርገን ለመመጻደቅም አይደለም፡፡ ይህን ቀን የምናከበረው ለሁለት ጉዳይ ነው፡፡ አንደኛው በትግል ውስጥ የኢሕአፓ አባል ሆነው ውድ ህይወታቸውን በመስጠት ክቡር መስዋእትነት የከፈሉ ጓዶቻችንን ለማስታወስና ለመዘከር ሲሆን÷ ሁለተኛው ለሀገራችንንና ለሕዝባችን ያለንን ጽኑ ፍቅርና ታማኝነት የበለጠ ለማረጋገጥ ነው፡፡ ኢሕአፓ ሲመሠረት ይዞ የተነሳው ዓላማ - የሕዝብ መብት መረጋገጥ÷ የዴሞክራሲ መስፈን÷ የነፃነት እውን መሆን እና መሰል ክቡር ዓላማዎች ገና እውን አልሆኑም፡፡ እንዲያውም አገራችን በትልቅ አደጋ ላይ ሕዝባችንንም በታሪኩ ደርሶበት በማያወቅ ታላቅ ችግር ውስጥ ወድቀዋል፡፡ የዛሬን በዓል የምናከብረው ሕዝቡን ባለመብት ለማድረግ ለመታገል ቆርጠናል ብለን ገና ከመጀመሪያው ለሕዝባችን የገባነውን ቃል ኪዳን ለማደስ ነው፡፡፡ በዘሬው ቀን ከእኛ ጋር በዓሉን ለማሳለፍ እዚህ የተገኛችሁ ወዳጆቻን ሁሉ እኛን መደገፋችሁ ÷ ትግሉን ማጠነካራችሁ ÷ ለሀገራችንና ÷ ለሕዝብ እየተደረገ ላለው ትግል አጋዥነታችሁን መግጸለጻችሁ ስለሆነ እንኮራባችኋለን፡፡ እዚህ ስለተገኛችሁም በድጋሚ እናመሰግናለን፡፡

የዛሬ 36 ዓመት ህልውና ያገኘው ኢሕአፓ በሀገራችን የመጀመሪያ ፖለቲካ ፓርቲ ነው፡፡ በወቅቱ በሥልጣን ላይ የነበረው ክፍል በሕዝብ ላይ ያደርስ የነበረውን በደል ይቃወሙ የነበሩ÷ ለሀገራች ን ለአ ትዮጵያ በጎ ለውጥ÷ የእድገት የብልጽግና ለውጥ÷ ሥረ ነቀል ለውጥ÷ እንዲመጣ ከልብ ይመኙ የነበሩ ወጣቶች ያቋቋሙት ድርጅት ነው፡፡ የበደሉን ክብደት የደህነነትና የኋላ ቀርነቱን መጠን በሚገባ ለመገንዘብ የቻሉ ወጣቶች ያቋቋሙት ነው፡፡ የሕዝብ መብት እንዲከበር መሬት ላራሹ እንዲሆን ድህነትና ኋላ ቀርነት ተወግደው አገራችን በእደገት ጉዞ እንድትራመድ የሚያስችሉ እርምጃዎች እንዲወሰዱ÷ ፖሊሲዎች እንዲወጡ ተማሪዎች÷ ወጣቶች በያደባባዩ ያቀረቡት ጥያቄና ያደረጉት ተቃውሞ በገዥው ክፍል በኩል ሰሚ በማጣቱ÷ እንዲያውም ምላሹ ይበልጥ አፈና ሆኖ በመገኘቱ ተደራጅቶ ከመታገል ውጭ የተሰበጣጠረ ተቃውሞ የትም ሊደርስ አለመቻሉን በመገንዘባቸው ነው በፖለቲካ ድርጅት ተደራጅተው ለመታገል የወሰኑት፡፡ ስለሆነም ኢሕአፓ የእነዚህ ወጣቶች የትግል ውጤት ነው፡፡ በትግል ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት የተመሠረተ ፓርቲ ነው ፡፡

የፖለቲካ ነፃነት እውን ሆኖ የሕዝብ መብት ሳይገደብ ሙሉ በሙሉ ተረጋግጦ ገባርነት ተወግዶ መሬት ላ ራሹ ተሰጥቶ፥ ድኅነት ኋላ ቀርነት ተቀርፈው ፥ በሃማኖቶች መካከል እኩልነት ሰፍኖ፥ በብሔረሰቦች እኩ ልነት ላይ የተመሠረተ የኢትዮጵያ አንድነት ተረጋግጦ፥ ሀገራችንም ከባዕድ ቁጥጥር ተላቃ ነፃነቷንና ሉዓላ ዊነቷን አስከብራ የምትነኖርበትን ሁኔታ ለመፍጠር ነበር የኢሕአፓ ዓላማዬ በሎ የተነሳው።

ኢሕአፓ የተመሠረተው በደልደላ መሬት አልነበረም ፥ ከተመሠረተ በኋላም የተጓዘበት መንገድ አልጋ ባልጋ አልነበረም። ብዙ አቀበትና ቁልቁለትን፥ ብዙ ኮረንኮች መንገዶችን ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፏል። የነበረ ው የተመክሮ ጉድለት፥ በየወቅቱ የደረሱበት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ከፍተኛ ፈተና ውስጥ ቢከቱትም ለሕዝ ብ ያለው ፍጹም እምነት መከታ ሆኖት፥ ጠንካራ መከላከያ ሆኖት ህውናውን ጠብቆ ቆይቷል። በየወቀቱና በየእየርከኑ የደረሰበትን ተካታታይ ፈተናዎችና ችግሮች በሕዝብ ፍቅርና አለኝታነት ተቋቁሞ ትግሉን ቀጥለ ◦እስከዛሬ አለ። ፓርቲው ሲመሠረት ሥርዓቱ የሚያፈናፍን ስላልነበር አባላቱን በኅቡዕ ለመመልመል፥ ደጋፊ ዎችን በኅቡዕ ለማሰባሰብ መዋቅሩንም በኅቡዕ ለመዘርጋት ተገዷል። ከዚያ በኃላ በተከታታይ የመጡት የደር ግና የወያኔ ሥርዓትም ከጥቅማቸውና ከሥልጣናቸው ውጭ ለሰው ልጅ ህይወት የሚሰጡት ዋጋና ክብር ስላ ልነበር ሥልጣን የሕዝብ የሚሆንበት ሥርዓት እንዲመሠረት ኢሕአፓ ከእነዚህ ሥርዓቶች ያካሄደው ትግል ከባድ መስዋእትነትን መጠየቁ አይቀሬ ነበር።

በ36 ዓመታት የኢሕአፓ ታሪክ ለሕዝብ መረጋገጥ ለአገር አንድነትና ሉዓላዊነት ለሰላምና ለፍትኅ ሲታገሉ ብዙ ብዙ አባላት የህይወት መስዋእትነት ከፍለዋል፥ አካለ ስንኩላን ሆነዋል፥ በየእስር ቤቱ ማቀዋል፥ ቤት ን ብረታቸውን አጥተዋል፥ ከሀገራቸው ተሰደዋል ። የሕዝብን ቁጣ ተተንርሶ የአዔውን መንግሥት አስወገዶ በ ጠመንጃ ኃይል ሥልጣን የያዘው ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ሥልጣን ለሕዝብ እንዲያስረክብ ኢሕአፓ በ መጠየቁ ተቃወሞ በማሰማቱና ትግል በማድረጉ በፓርቲው ላይ ጦረነት አውጆበታል። አረመኔያዊ በሆነ መን ገድ በስፋት ባካሄደው ቀይ ሽበር በርካታ መተኪያ የማይገኝላቸው አባላቱ እንዲሁም ሌሎች ብርቅዬ ዜጎች ተገድለዋል፥ በየአደባባዩ ሬሳቸው ተጠሏል፥ በአስር ቤቱ ኢሰበአዊና ሰቆቃዊ ድርጊት ተፈጽሞባቸዋል፥ ክብ ርናቸው ተደፍሯል፥ሰብእናቸው ተዋርዷል ። ኢሕአፓ የጠባብ ብሔረተኞ ች ድርጅቶች ን የመገንጠል ስ ውር ዓላማ በማጋለጡ፥ ድርጅቶችን በመቃወሙና በመታገሉ ሁሉም ተረባርበውበታል፥ ከፍተኛ ወታደራ ዊ ጥቃት አድርሰውበታል በዚህም በርካታ የኢሕአፓ አባላት ህይወታቸውን መስዋእት አድርገዋል። በጠመን ጃ ኃይል ወያኔ ሥልጣን ላይ ሲወጣ የወያኔን ከፋፋይነት ፖሊሲ ፥ የኤርትራን መገንጠልና እንዲሁም አምባ ገነን ሥርዓት ለማስፈን ሲያውጠነጥን የነበረውን ሴራ በማጋለጡና በመቃወሙ ፥ ሰፊ ሕዝብ ተሳታፊ የሚሆ ንበት የሽግግር መንግሥት እንዲመሠረት በመጠየቁ ወያኔና ተባባሪዎቹ አጥቅተውታል። ፀረ ኢትዮጵያ የሆ ነው የወያኔ ቡድን ወደ ሥልጣን ሲመጣም ይህ ቡድን የሚያደርሰውን ከፍተኛ አደጋ ኢሕአፓ ለሕዝብ በማ ጋለጡና ወያኔን በመታገሉ ከወያኔና ከተባባሪዎቹ ከባድ ጥቃት ደርሶበታል። ብዙ መተከያ የማይገኝላቸው አ ባሎቻችን ህይወታቸውን አጥተዋል፥ በወያኔ የጉድጓድ አስር ቤቶች ማቅቀዋል፥ እያማቀቁም አሉ፥ በዙዎቹ መዳረሻቸው ጠፍቷል። የኢሕፓን አርማ አንግበው ፥ የድርጅት አባል ሆነው መታገል ጀምረው፥ በኋላ ወኔ የከዳቸው፥ የግል ጥቅምና ምኞት ከሀገርና ከወገን ጥቅም የበለጠባቸው ከሃዲዎች ከኢሕአፓ ተለይተው አን ጃ አቋቁመው ከጠላት ጋር አብረው ኢሕአፓን አቁሰለዋል። የብዙ ውርቅዬ ልጆችን ህይወት ቀጥፈዋል። አስቀጥፈዋል።

የዛሬውን ቀን የምናከብረው በትግል ውስጥ ወድ ህይወታቸውን መስዋእት የከፈሉ አካላቸውን ያጡ በየእስር ቤቱ እየማቀቁ ያሉ አባሎቻችንን በመዘከር ነው። እነዚህ ለእኛ ጀግኖቻችን ናቸው። አንዳንድ ኢሕአፓን የ ሚቃወሙት ወገኖች እንደሚሉት የሞኝ ሞት የሞቱ አይደሉም፤ በተሳሳተ መስመር ያለ ምክንያት ያለቁ ወ ጣቶችም አይደሉም። እነዚህ ወጣቶች ይህን ሁሉ መከራ የተቀበሉት፥ ይህን ሁሉ መስዋእትነት የከፈሉት ለ ሚወዷት ሀገራቸውን ለሚወዱት ሕዝባቸው ራስን አሳልፎ ከመስጠት በላይ ምንም ክቡር ነገር እንደሌለ በማ ወቃቸው ነው። አምባገነኖችን ታግለው ለሕዝባቸው መብት ለማጎናጸፍ ነው፥ አገር ሻጮችን ከፋፋዮችን ታ ግለው የኢትዮጵያን ልዕልና ለማረጋገጥ ነው። ከዚህ የበለጠ ጀግንነት ምን አለ? ለሀገርና ለወገን ከመሰዋት በ ላይ። ጀግኖች መከበር አለባቸው፥ ጀግኖች መዘከር አለባቸው። ጀግኖች አባቶቻችን ራሳቸውን አሳልፈው በ መስጠት ይችን አገር ከጠላት ተከላክለው አቆይተውናል። ከኢሕአፓ አባላት ውጭ በርካታ አገር ወዳድ ወገ ኖች የወያኔን ሥርዓት ሲፋለሙ ህይወታቸውን አጥተዋል። እነዚህን ጀግኖች ማክበር፥ መዘከር አለብን። ሀገ ራችን ጀግና ልታፈራ የምትችለው ጀግኖችን ስናከበርና ስንዘክር ብቻ ነው። በተለይም አሁን በሥልጣን ላይ ያለውን አረመኔ መንግሥት በጽኑ ታግሎ፥ መሰዋእትነት ከፍሎ ሊያስወደግድ የሚችል ጀግና ትውልድ፥ ጀ ግና ወጣት እንዲኖር ከፈለግን፥ ጀግኖቻችንን ማክበር፥ ጀግኖቻችን ማስታወስ፥ ጀግኖቻችንን መዘከር አለብ ን።

36 ዓመቱን ያስቆጠረው ኢሕአፓ የጀመረው ትግል ዳር ባለመድረሱ ትግሉ ዋጋ እንዳልነበረው ፥ የተከፈለ ው መስዋእትነት ሁሉ ሜዳ እንደቀረ አድርገው የሚቆጥሩ አሉ። እርግጥ ነው 36 ዓመት ረዥም ዓመት ነው፥ የአንድ ጎልማሳ ሰው እድሜ ነው። ከሕዝባዊ ትግል አንጻር ሲታይ ግን ብዙ ነው የሚባል አይደለም። ኢሕአ ፓ የሚታገለው ለሕዝብ ነው፥ የሚታገለውም ሕዝብን ይዞ ነው። የኢሕአፓ ትግል የሚያበቃው፥ የኢሕአፓ አባላት መሰዋእት መሆን የሚያቆሙት ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት ሲሆን ብቻ ነው። ስለሆነም ኢሕአፓ የሚ ያካሂደው ሕዝባዊ ትግል ነው። የሕዝባዊ ትግል ውጤት በጊዜ ሊተመን የሚችል አይደለም። ብዙ ውስብስብ ጉዳዮች እድሜውን ሊያስረዝሙ ወይም ሊያሳጥሩ የሚችሉበት ሁኔታ አለ። በአንዳንድ ሁኔታዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ትግል ግቡ ላይ ደርሶ ለፍሬ ሲበቃ በአንዳንድ ሁኔታዎች ትግሉ ዳር ለመድረስ የብዙ ትውልዶች እድሜ የጠየቀ መሆኑ ከዓለም ተመክሮ መረዳት እንችላለን። ሕዘባዊ ትግሉ መቼ ሊያሸንፍ ይችላል ለሚለ ው ጥያቄ እርግጠኛ መልስ መስጠት ባይቻልም የኋላ ኋላ በእርግጥ አሸናፊ ሊሆን እንደሚችል ግን ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ የለንም። ኢሕአፓ ያሰለፈው ትግል 36 ዓመታት ቢፈጅም፥ የተነሳበት ዓላማ እስካሁን ግቡን ባይመታም ለሕዝባዊ ትግሉ ያደረገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ለመሆኑ ሁሉም ዜጋ የሚያምንበት ነው።

- የውጭና የውስጥ ጥቃትን ተቋቁሞ፥ የድርጅት ህልውናን ጠብቆ ትግልን ማካሄድ ራሱ አንድ አስተ ዋጽኦ ነው። ግምባሩን ሳያጥፍ፥ ጥቅም ሆነ ሹመት፥ ዝና ሆነ ክብር ሳያታልለው ቃል ኪዳኑን ጠብቆ አምባገነኑን መታገል መቻሉ ለሕዝባዊ ትግል የተደረገ አስተዋጽኦ ብንል ማጋነን አይሆንብንም።
- የሕዝብ መብት መከበር፥ የብሔረሰብ እኩልነትና አንድነት፥ የፆታና የሃይማኖት እኩልነት፥ የፖለቲ ካ ድርጅት አስፈላጊነት፥ ስለ ዴሞክራሲ አስፈላጊነት፥ ስለ ሕዝብ ኃያልነት ኢሕአፓ ባካሄደው ረዥ ም ትግልና በከፈለው መስዋእትነት ሕዝብ ግንዛቤ እንዲያደርግ አድርጓል። ዛሬ ማንም የሕዝብ ክፍ ል አምባገነን ኃይልን የሚያስተናግድበት ሁኔታ የለም።

- በወሳኝ ወቅቶች በተለይም የአምባገነን አገዛዝ ለማቆጥቆጥ ሲንሰራራ ኢሕአፓ የታገለባቸው መርሆ
ዎች ትክክለኝነታቸው ዛሬ የሚያከራክር አይመስለንም። በደርግ ጊዜ በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥ
ት ምትክ ኢሕአፓ ያቀረበው የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ ተግባራዊ ቢሆን ኑሮ ፥ በወያኔ ገ
ዜም ወያኔ የቀልድ የሽግግር ጉባዔ ሲጠራ ሰፊዎን ክፍል ያካተተተ ጉባዔ የሽግግር መንግሥት ይ
ቋቋም የሚለዉት ጥያቄዎች ተቀባይነት አግኝተው ትግል ቢካሄድባቸው ኖሮ አምባገነኖች በኢትዮ
ጵያ ሕዝብ ጫንቃ ተቀምጠው ባልቀለዱም ነበር።

በረዥም የትግል ታሪኩ ኢሕአፓ ለበርካታ ጊዜያት ከወዳጆቹ ወቀሳና ምክር፥ ህልውናውን ከማይፈልጉ ተ
ቀናቃኞቹ ወገዛና ኩነናም ደርሶበታል። በመሠረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ከኢሕአፓ አቋም ጋር የሚስማሙ
ኢሕአፓን እንደ ወዳጅ ድርጅት የሚቆጥሩ ክፍሎች ስህተቱን ድክመቱን በጥሞና ሲጠቁሙት፥ ምክር ሲለ
ግሱት የኢሕአፓ ህልውና የሚያስፈራቸው የጠላት ወገኖች ደግሞ በሀሰትና በአልቧልታ የተሞሉ ክሶችንና
ወገዛዎችን በማኸጎድጎድ ኢሕአፓ ከሕዝብ እንዲነጠል ፈራርሶና ኢምንት ሆኖ እንዲቀር ጥረዋል፥ ኳትነዋ
ል። ፍጹምነት የአምላክ ብቻ ስለሆነ ኢሕአፓ ፍጹም ነኝ አልተሳሳትኩም አልሳሳትም ብሎ አያውቅም። በ
ትግሉ ውስጥ ስህተቶችን ሠረቷል የተሠሩ ስህተቶች ግን በቅንነት የተሠሩ በመሆናቸው በወቅቱ አርሚቸዋ
ል። የሠራውን ስህተቶች በድፍረትና በቅንነት ይፋ አድርጓል። ኢሕአፓ ለጠላቱም ለወዳጁም ለማሳወቅ የ
ሚፈልገው በቅንነት የቀረቡትን ወቀሳዎች እየተቀበለ፥ ስህተት የተባሉትን እያረመና እያሻሻለ፥ ማንነቱን ለ
ማጥቆር፥ ትግሉን ለማኮሸትና ህልውናውን ለማጥፋት የሚሸቀዳደሙትን እየተከላከለ ትግሉን ይበልጥ አጠና
ክሮ ለመቀጠል ቆርጦ የተነሳ መሆኑን ነው።

በቅርቡ ትግሉን አስመልክቶ ብዙኃኑ የኢሕአፓ አባላት ከሚያምንበት የተለየ አቋም የነበራቸው፥ በነበራቸው
መድረክ ተከራክረውና ተወያይተው ብዙኀኑን አሳምነው በዴሞክራሲያዊ መንገድ አቋማቸውን የድርጅት አ
ቋም ማድረግ ወኔ ያጠራቸው ጥቂት ግለሰቦች መድረኩን ረግጠው፥ ከኢሕአፓ ተለይተው በስሙ ላይ ዴሞ
ክራሲያዊ የሚል ቅጽል ለጥፈው በኢሕአፓ ስም መንቀሳቀስ ጀምረዋል። ከኢሕአፓ መለየትም ሆነ ተደራ
ጅቶ መንቀሳቀስ መብታቸው ቢሆንም ተመሳሳይ ስም በመያዝ በሕዝቡ ውስጥ ውዥንብር ለማስፋፋት እያደ
ረጉ ያሉት ጥረቶች ጠላትን ይጠቅማል እንጂ የሕዝብን ትግል አያገለብትም። ለዚህም በታሪክ የሚጠየቁበት
ይሆናል። ተመሳሳይ ችግሮችና ፈተናዎችን በየገዜው የተቋቋሙ፥ ለማናቸውም አደጋ የማይበገሩ ግምባራች
ወን የማያጥፉ፥ ተስፋ የማያስቆርጡ አባላቱ ይህን አነስቶኛ ችግር ተቋቁመው አሁንም ትግሉን ከመቸውም
ጊዜ በላይ አጠናክረው፥ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን ከጥፋት ለማዳን በሚደረገው የሞት የሽረት ትግል
በግምባር ቀደም ወያኔን በጋተር/ በመቋቋም ላይ ይገኛሉ።

የሀገራችንን ሁኔታ መለስ ብለን ስናይ አገራችን በጣም አደገኛ ሕዝባችንም በጣም አሳዛኝ ሁኔታ ላይ መሆኑን
እንረዳለን። ሕዝባችን በታሪኩ ደርሶበት የማያውቀው በደልና ጭቆና ደርሶበታል። አገሩን እንደ አገር፥
እንደ ኢትዮዮጵያ ለማቆየት አሱም እንደ ሕዝብ፥ እንደ ኢትዮጵያዊ ለመቆየት ከፍተኛ ፈተና ውስጥ ወድቋ
ል። የወያኔ ጠባብ ቡድን በሕዝብ ጫንቃ ላይ ተቀምጦ ሕዝባችንንም አገራችንም ወደ መቀመቀመቅ ለማው
ረድ ሌት ተቀን እየሠራ ነው። የሕዝብ መብት ታፍኗል፥ ድህነት ከመቸውም ጊዜ በላይ ተሰፋፍቶ ይገኛል፥

ሕዝባችን በዘርና በሃማኖት ተካፋፍሎ በጠላትነት እንዲተያይ  አንዱ ባንዱ  ላይ እንዲነሳ ግፊት እየተደረገ በት ይገኛል፥ የትምህርት ይዞታው አሽቆልቁላል፥ ተላለፋፊ፥ ቀሳፊ በሽታዎች ተስፋፍተዋል፥ በረሃብና በጠኔ ማለቅ የኢትዮጵያውያን ዓይነተኛ መለያ ሆኖ ቀጥሏል፥ የሀገሪቱ ሀብት ሥልጣን ላይ በተፈናጠጡ ስግ ብገቦች ፥ ከጥቅማቸው በስተቀር ለአገር ለወገን ደንታ የሌላቸው ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ያላቸው ሹመኞች እየተዘረፈ ነው። የኑሮ ውድነቱ፥ ከቤት ንብረት መፈናቀሉ፥ ግቦኞነቱ ዘረፋው ሕዝቡን አስመርሮታል። ጨ ቋኙ ቡድን ሕዝባችንን እየጨቆነና እየበዘበዘ ያለው ግፍ አልበቃ ብሎት የአገራችንን መሬትና ክብር ለባዕድ እየቸረቸረ እንድትዋረድ አድርጓታል። ከጥቂት ዓመታት በፊት የአባይ ውሃን አጠቃቀም አስመለክቶ ከግብፅ  ጋር ያደረገው ምሲጢራዊ ስምምነት ሁላችንም የምናውቀው ነው:: በቅርቡ በወሰን ላይ ያለውን ሰፊ ለምና የርሻ መሬት ለሱዳን መሸጡ የአደባባይ ሚስጢር ነው። ከአሜሪካን መንግሥት ጥቅም ለማግኘት፥ በሥልጣን  ላይ ለመቀየት መከላከያ ለማግኘት የኢትዮጵያን ብርቅዬ ልጆች ወደ ሶማሊያ ልኮ የሰው ህይወትና የገንዘብ  ግብር እንዲከፈል ከማድረጉ በላይ ኢትዮጵያ በአካባቢው አረብና እስላም አገሮች በጠላትነት እንደትታይ እ ያደረጋት ነው።  የአሜሪካን ፍላጎት ለማሟላት የወጭ ዜጎች ባገራችን ውስጥ በምስጢር እስር ቤት ታስረው ሰቆቃዊ ድርጊት እንዲፈጸምባቸው በመፍቀድ አገራችንን ዳግማዊ ጓንታናሞ የሚል ቅጽል ስም እንድታገኝ አድረጓታል። ሀገራችንን በዓለም ኅብረተሰብ እንድትዋረድ አድርጓታል። ባጠቃላይ ሀገራችን ለወያኔና ለጥቂ ት የጥቅም ተካፋዮቹ መፈንጫና መዝናኛ ለብዙኃኑ ደግሞ የስቃይና የመከራ አስር ቤት ሆናለች።::

እኛ ኢትዮጵያውያን ይህን ሕዝባችንን እያሰቃየ  ሀገራችንንም እያዋረደ ያለውን አጥፊ ኃይል ታግለን ማስወ ገድ አለብን። ጭቆናን አለመቀበል አገርን ከውርደትና ከስቃይ መከላከል የእኛ  የኢትዮጵያውያን መለያችን  ነው፥ ካባቶቻችን የወረስነው ቅርስ ነው። ሕዝባችን በታሪክ ከደረሰበት ሰቃይ ሁሉ በከፋ ስቃይ ውስጥ እየኖ ረ፥ ከአንስሳ ኑሮ በማይሻልበት ውስጥ እንዲገባ እየተደረገ፥ ሀገራችን በክፍፍል ተንኮል ህልውናዋ ፈተና ውስ ጥ ገብቶ እያለ ፥ የሀገራችን ሀብት በስግብግቦች እየተዘረፈ፥ ለባዕዳን አሳልፎ እየተሰጠ ሁኔታውን በእርምሞ  ማየትና ከትግል መራቅ የኢትዮጵያውያን ባህሪ አይደለም፥ በታሪክም በትውልድም ያስጠይቃል።

ይህ አምባገነን ኃይል ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ባለይ በሕዝብ ተጠልቶ፥ከሕዝብ ተነጥሎ ይገኛል። ከሕዝብ ስለተ ነጠለም ደካማ ነው። ሕዝብ ሰላማዊ ተቃወሞ ሲያሰማ እያካሄደ ያለው የጅምላ ጭፍጨፋ፤ የመብት ረገጣ ፥ እንዲሁም የሚያካሂዳቸው የአፈና ተግባሮች ድክመቱን እንጂ ጥንካሬውን የሚያሳዩ አይደለም። የሕዝብ ኃ ይል ከተሰባሰበ፥ የሕዝብ ትግል ከተጠናከረ ይህን ኃይል ማስወገድ ይቻላል።

ምን ማድረግ አለብን የሚለው ጥያቄ መጠየቅ ያለበት ነው። የወደፊቱን ለመተለም ያለፍንበትን በጥሞና መ መርመርና መገምገም የግድ ይሆናል።  በቅድሚያ አንዳንድ የተዛቡ አመለካከቶች መስተካከል ይኖርባቸዋል: :

ከሁሉ በፊት ይህ አምባገነን ሥርዓት በልምናና በምልለላ፥ በድርድርና በውይይት፥ በሰላማዊ መንገድ ከውስ ጥ ሆኖ ቀስ ቀስ በቀስ በመቀየር ወዘተ... ለሕዝብ ሥልጣን ያስረክባል የሚለው አመለካከት መወገድ አለበት: : ይህ ሊሆን እንደማይችል ባለፉት 18 ዓመታት የተደረጉት ጥረቶች  በተለይም በግንቦት 97 ምርጫ ግልጽ አድርገዋል። ይህ መንግሥት ሊወገድ የሚችለው በተጠናከረ ሕዝባዊ ትግል ብቻ ነው። በሰላምና በድርድር

ሊለቅ ይችላል የሚል እምነት በህሊናችን የሚመጣ ካለን በቅድሚያ መገንዘብ ያለብን ይህ ዘረኛና አጥፍፊ ሥርዓት በሰላም ሥልጣኑን ለሕዝብ ሊያስረክብ የሚችለው በሕዝብ ኃይል ሲገደድ ፤ ሕዝብ ኃያል መሆኑን ሲገነዘብ ብቻ ነው።

ሁለተኛ ይህን መንግሥት ሊያስወግዱት የሚችሉት የባዕድ መንግሥታት ብቻ ናቸው የሚለውም አመለካከ ት መወገድ አለበት። ባለፈው አስራ ስምንት ዓመታት በባዕድ አደባባዮች ያሰማነው የተቃውሞ ድምፅ ለመን ግሥት ባለሥልጠናት ለምክር ቤት ተመራጮች ያቀረብነው አቤቱታ የጻፍነቻው ደብዳቤዎች ሰሚ ጆሮ አ ላገኙም። የባዕዳን መንግሥታት በቅድሚያ የሚያተኩሩት የራሳቸውን ጥቅም እንጂ የሕዝብ በደልና ስቃይ አለመሆኑ የቡሽ አስተዳደርና የወያኔ ዘረኛ ሥርዓት ያላቸው ወዳጅነት ገልጽ አድርጎ ያሳየናል። ለራሳችን ወ ሳኝ የምንሆነው እኛው ነንና አምባገነንነት ለማስወገድ የራሳችንን ኃይል ከማጠናከር ውጭ፥ ጠንካራ ሆነን ከመገኘት በቀር ሌላ አማራጭ ሊኖር አይችልም። የባዕዳን ተጽእኖ የአምባገነኑን ቡድን ከሥልጣን ለማስወ ገድ በሚደረግ ላይ አስተዋጽኦ አይኖረውም ማለት አይደለም ፥ ይኖረዋል ፥ ጥረቱ በዚህ በኩልም መቀጠል አለበት ። ግን ባዕዳን ራሳቸው እኛን ሊሰሙ የሚችሉት እኛ ተጠናክረን ከተገኘን ብቻ ነው። ስለዚህ ራሳች ንን ማጠናከር አለብን።

እንዴት እንጠናከር የሚለው ሌላው ትክክለኛ ጥያቄ ነው። በቅድሚያ ሕዝብ መደራጀት አለበት። ሕዝብ ተደራጅቶ የትግሉ ተሳታፊ መሆን አለበት። የፖለቲካ ድርጅቶች ሕዝቡንና ትግሉን መርተው ለድል ማብቃት ኃላፊነት ቢኖርባቸውም ሕዝብ በስፋት በትግሉ ካልተሳተፈ ትግሉ ግቡን ሊመታ አይችልም። ድር ጅት ያለ ሕዝብ ተሳትፎ ብቻውን ቀፎ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ለትግሉ ዋስትና ሊሰጥ የሚችል ሌላው ዐቢይ ጉዳይ ደግሞ በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል እንዲሁም ሰፋ ሲል በተደራጀው ሕዝብ መካከል ሊኖር የሚገባው የጋራ እንቅስቃሴና የኅብረት ትግል ነው። እስካሁን የተሞከሩት የኅብረት እንቅስቃሴዎች አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ ተግባሮችን ቢያከናውኑም ትግሉን ወደ ግብ ከማድረስ እንፃር ውጤት ሊያስገኙ አልቻሉም ። የድርጅቶች ኅብረት አለመሳካት ብዙ ምክንያቶች ሊደረደ ሩ ቢችሉም ዋናውና ዐቢዩ ምክንያት የወያኔ አምባገነንነት እንዴት ይወገድ በሚለው ላይ የጠራና ተመሰሳይነ ት ያለው አቋም አለመኖሩ ነው። የተጠናከረ የድርጅቶች ኅብረት አለመኖር ተሰፋ ሊያስቆርጠን አይገባም። በትግላችን ህልውና እንዲያገኝ ከማድረግ ወደኋላ ማለት የለብንም። እስከዚያው ድረስ ግን ሁላችንም ተገተን ትግሉን በማጣጧፍ ሀገራችንን ከጥፋት ማዳን አለብን።

በኢሕአፓ በዚህ በኩል የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ነው ። የወያኔን ስለላና አፈና እየተቋቋመ ሲያስፈልግም ተገቢ መስዋእትነት እየከፈለ በአገር ቤት ታጋዩን የማደራጀትና አደራጅቶ የማታገል ሥራውን አጠናክሮ ቀጥሏል። በሳምንት ሶስት ጊዜ በሚተላለፈው የፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ ሕዝባችን የመረጃ ፍላጎቱ የተሟላ እንዲሆን፥ የትግሉን አቅጣዎችንም እንዲገነዘብ ለማድረግ ጥረቶች እያደረጉ ነው። ተመሳሳይ አቋም ካሏቸው ና የትግል አጋር ከሆኑት ወገኖችና ድርጅቶች ጋር የተባበረ እንቅስቃሴና ትግል ለማድረግ ጥረቶች እያደረገ ነው። ሁለ ገብ ትግሉን አጠናክሮ ለመግፋትም የሚቻለውን ጥረት እያደረገ ነው።

ዴሞክራሲ አውን ሆኖ ፥ ሕዝባችን በሀገሩ ላይ ባለመብት ሆኖ ፥ ባለ ሀገር ሆኖ፥ የሀገራችን አንድነት ተረጋግጦ ፥ ሉዓላዊነቷ ተከብሮ ፥ ረሃብና በሽታ ተወግደው መሰደድ ቆሞ ሁላችንም የኢትዮጵያ ዜጎች በተድላና በደስታ የምንኖርበት ሁኔታ እንዲፈጠር ከፈለግን ብዙ ውጣ ውረድና መስዋእትነት የሚጠይቀውን ትግል ማድረግ መቻል አለብን ፡፡ እኛ የኢሕአፓ አባላት በዚህ በኩል የሚቻለንን እያደረግን ነው፡፡ ትግሉ ተጠናክሮ ግቡን እንዲመታ የእናንተን ትብብርና እርዳታ እንፈልጋለን፡፡ በሕዝብ ኃይል በሕዝብ አቸናፊነት እናምናለንና እጅ ለእጅ ተያይዘን በኅብረት ትግሉን ካጠናከርና ባጭር ጊዜ ውስጥ ፍላጎታችንና ምኞታችን እውን ሊሆን እንደሚችል አንጠራጠርም፡

በዓላችንን ለማክበር የተደረገላችሁን ጥሪ በቀበል ስለተገኛችሁልን በድጋሜ ከልብ እናምግናለን፡፡

ኢትዮጵያ ሀገራችን በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኖራለች!!!!